የሰ.መ.ቁ. 21790
ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ቱጃሬ ደጀኔ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ተካ ሰፋራ

2ኛ. አቶ ጥላሁን ሰፋራ

3ኛ. አቶ ፈይሳ ሰፋራ

4ኛ. አያንቱ ሰፋራ

5ኛ. ከፋኔ ሰፋራ

6ኛ. ተስፋይ ሰፋራ

7ኛ. አለማየሁ ሰፋራ

8ኛ. ፋጡማ ሰፋራ

9ኛ. ወርቅ ደራሳ

10ኛ. አልማዝ ሰፋራ


ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

11ኛ. አስናቀች ሰፋራ

12ኛ. ደጀኔ አዱኛ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 326124 በ21/08/2013 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፤የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 376545 ጥቅምት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሲናና ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን 11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች በቅደም ተከተል 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች፤ የአሁን አመልካች እና ከ2- 10ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገቦች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ:- የአሁን 11ኛ የ12ኛ ተጠሪዎች እና 11ኛ ተጠሪ የ12 ተጠሪ ባለቤት ለ1ኛ ተጠሪ ደግሞ እህት ናቸው፣ አባታችን አቶ ሰፋራ ሆርዶፋ መስከረም 24/2011 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፤ አባታችን 8 ልጆች አሉት፤አዋሳኞቸው በክሱ ላይ የተገለጸውን 5 የእርሻ መሬት እና አንድ 20 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት የአባታችን ንብረት በመሆኑ ተጠሪዎች ድርሻቸውን እንዲያካፈሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን 11ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አባታችን በህይወት እያለ በክሱ ተ.ቁ 1፣ 2 እና 3 ላይ ያለው ይዞታ ለአሁን አመልካች በስጦታ ሰጥቷል፣ በክሱ ላይ በተ.ቁ 4 እና 5 ላይ የተገለጹት ይዞታዎች ደግሞ ለ9ኛ ተጠሪ ከሚች ጋር በህይወት እያሉ በባልና ሚስትነት ያፈሩት እና ጋብቻቸው ሲፈርስ ለ9ኛ ተጠሪ ድርሻ የሆነ በመሆኑ የውርስ ንብረት አለመሆኑን በመግለጽ የ1ኛ ተጠሪ ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

12ኛ ተጠሪ የጽሁፍ መልስ ለማቅረብ በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከ2ኛ-7ኛ እና 8ኛ -10ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ሲከራከሩ ተጠሪዎች የሚች ወራሾች ነን፤1ኛ ተጠሪ በክሱ ውስጥ የጠቀሰው 7 ጥማድ ከሚች ጋር ጋብቻው ሲፈርስ ለባለቤቱ የደረሳቸው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ሲከራከሩ ሟች አያቷ መሆኑን በመግለጽ ሟችን 1ኛ ተጠሪ አባሯቸው አመልካች በማስጠጋት በ2005 ዓ.ም በክሱ በተ.ቁ 1፣2፣3 እና 6 ላይ የተገለጹትን ይዞታዎች በስጦታ ተሰጥቷቸው በሚመለከተው አካል አስመዝግበው የያዙት መሆኑን ገልጸው ማመልከታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን የቀረበለት ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ወደ ባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ተጠይቆበት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በመ.ቁ. 29995 በ14/5/2012 ዓ.ም በነጥብ ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱን ከመዝገቡ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ እና ከሚመለከተው አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት አድርጎ አመልካች ሟች አያቷን ስትንከባከብ እና ስትጦር የቆየች ቢሆንም አመልካች ከ11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ልጅ እና የመንግስት ሰራተኛ በመሆኗ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እያሉ ለአመልካች ስጦታ መደረጉ አዋጅ ቁጥር 130/1999 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 5/5/ ፣ 3/1/ እና 9(2) የሚቃረን ነው፤ የ9ኛ ተጠሪ በማስረጃ አልተረጋገጠም፣ በመሆኑም ለአመልካች የተሰጠው የስጦታ ውል ሊሰረዝ ይገባል፤ ለክርክር መነሻ የሆኑት የውርስ ይዞታዎች አመልካች፤ ከ1ኛ-8ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች እኩል ይካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሟች በህይወት እያለ ከአመልካች ጋር አብረው ሲኖሩ አመልካች ስትጦረውና ስታሳክመው ሟች ወደ አስተዳደር አካል በመሄድ በመሬቱ ላይ ያለውን የመጠቀም መብት በስጦታ በፍላጎቱ ለአመልካች የሰጠ ስለሆነ ህጋዊ ነው፤ ስለሆነም በአመልካች የተሞላው የይዞታ ማሳ ኮድ 1090፣ 1091 እና 1092 የውርስ ይዞታ አይደሉም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ከ1ኛ -5ኛ ያሉ ተጠሪዎች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ለአመልካች የተሰጠው ስጦታ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾችን መብት የሚጋፋ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2439/1/ እና 3 እንዲሁም 939 የሚቃረን ነው፤ ስለሆነም በአመልካች እጅ ተመዝግቦ የሚገኙት ይዞታዎች በውርስ ይዞታ ላይ ተጨምሮ ከመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ጋር እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ሟችን ሲንከባከቡና ለረዥም ጊዜ ሲጦሩ በመቆየታቸው ምክንያት ሟቹ አሁን ክርክር ያስነሳውን 7 ጥማድ መሬት በሙሉ ፍላጎታቸው ለአመልካች በስጦታ እንደሰጧቸውና በሚመለከተው አካል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አስመዝግበው ሲጠቀሙ መቆየታቸው ተረጋግጧል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ከጭብጥ ውጭ በመውጣት ያለማስረጃ ውሳኔ መስጠታቸው ስህተት ነው፤ ለአመልካች የተሰጠው ስጦታው ህጉን ተከትሎ የተሰጠ ነው፣ ክርክሩ የውርስ ድርሻ መጠን ሳይሆን ሟች በህይወት እያለ በስጦታ ያስተላለፈውን ንብረት በተመለከተ በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2439 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፤ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን መሬት የያዙት አባታቸው በህይወት ሳሉ ተጠሪዎች ባልካዱበት ሁኔታ ስጦታ የሰጣቸው መሆኑን በተረጋገጠበት ሁኔታ በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች የውርስ ነውና ከውርስ ንብረት ጋር ይቀላቀል የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ከ1ኛ-5ኛ ተጠሪዎች የካቲት 29/2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አባታቸው ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ይዞታዎች በስጦታ አልሰጠም ሰጥቷል ቢባል እንኳን በ90 ዓመታቸው የተሰጠ በመሆኑ ስጦታው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ እና ከሟች ጋር አብረው በመሆን እየጦሩ እና ከመሬቱ ሲጠቀሙ አልነበሩም፤ ይዞታው በአመልካች ተመዝግቧል በማት የቀረበው ሰነድ ሀሰተኛ ነው፤ የስጦታ ውሉ በግራቀኙ የስጦታ ተዋዋዮች ያልተፈረመ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በመሆኑም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሰኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

6ኛ፣ 8ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የመንግሰት ሰራተኛ ሲሆኑ ሟች አባታቸውን አልጡም፤ ሟች ለአመልካች ስጦታ አልሰጠም፤ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ለአመልካች ይሰጥ መባሉ ተጠሪዎችን ከውርስ መንቀል ነው፤ አመልካች እንደ አንድ የቤተሰብ አባል የሚካፈሉ እንጅ ብቻቸውን ይዞታውን ጠቅልለው የሚወስዱበት የህግ አግባብ የለም፤ በመሆኑም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሰኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

7ኛ እና 11ኛ ተጠሪዎች በቀን የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ሟች አባታቸው ከመሞታቸው በፊት ይዞታውን ሲንከባከቡዋቸው ለነበሩት አመልካች በመስጠት የሟች የመጠቀም መብታ ተቋርጦ የቆየ እና አመልካች ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት ቆቶዋል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነ የውርስ ንብረት ድርሻችን ሊጠበቅልን ይገባል፤ በመሆኑም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሰኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ለ12ኛ ተጠሪ መጥሪያ ስለማድረሳቸው ያቀረቡት ማረጋገጫ ባለመኖሩ መጥሪያው ለተጠሪ ያልደረሰው በአመልካች ጉድለት እንደሆነ ተቆጥሮ በ12ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 70(መ) እና 199(1) መሰረት ተሰርዟል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በግራ ቀኙ በስር ፍ/ቤት የተደረገውን አጠቃላይ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጡ ውሣኔዎችን እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው 1ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በአሁን 11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የውርስ መሬቶችን ይዘው ስለሚገኙ ድርሻዬን ያካፍሉኝ የሚል የነበረ እና 11ኛ ተጠሪ በእጄ ንብረቱ የለም ብለው መከራከራቸው፣ አመልካችን ጨምሮ ከ2ኛ - 9ኛ ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት ቀርበው በዋነኝነትም አመልካች የተወሰነው መሬት በስጦታ የተሰጣቸው በመሆኑ የውርሱ ሀብት ነው ተብሎ ሊከፋፈል አይገባም በማለት መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም የክልሉ አርሶ አደር በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብቱን በስጦታ ለማስተላለፍ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 9(5) እንደተመለከተው ለቤተሰቡ አባላትና ለልጆቹ ብቻ ሲሆን እነዚህ ሰዎች በስጦታ ውሉ አግባብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የቤተሰብ አባላቱ በመሬቱ ገቢ የሚተዳደሩ ወይም ሌላ ገቢ የሌላቸው መሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባ ሲሆን ስጦታ የሚሰጣቸውን ልጆች አስመልክቶም ሌላ መሬት የሌላቸው መሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባ መሆኑ የድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት ያሳያል፡፡በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/16፡- “ የቤተሰብ አባል ማለት ከባለይዞታው የተወለዱ ልጆች ወይም ሌሎች መተዳደሪያ ገቢ የሌላቸውና በቋሚነት ከባለይዞታው ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው፡፡” በሚል የቤተሰብ አባል ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ሟች ሰፈራ ሆርዶፋ ልጆቹ ሊጦሩትና ሊያሳክሙት ስላልቻሉ አመልካች ወስዳቸው ስትጦራቸው እና ስትንከባከባቸው የነበረ መሆኑ በዚህ ምክንያትም አመልካች የቤተሰብ አባል ናቸው በሚያሰብል መልኩ ተቀብለዋቸው ቀበሌ ድረስ በመሄድ በይዞታው ላይ ያላቸውን ድርሻ በስጦታ ያስተላለፉላቸው መሆኑ በምስክሮች መረጋገጡን ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት ስልጣን ያላቸው ስር ፍርድ ቤቶች በዋነኝነትም የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሳኔያቸው ላይ አመልክተዋል፡፡አመልካች በስጦታ ያገኙትን የገጠር እርሻ መሬት ከሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ጋር እኩል እንዲወርሱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና በሰበር ሰሚ ችሎቱ የተወሰነው ደግሞ የስጦታ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ.939(1) አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾችን ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው መሆኑን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በማመልከት በመሆኑ በዚህ አግባብ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን መብት የሚያጣብብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 326124 ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ/መ/ቁ/ 37/6545 በ16/02/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

አ/መ                                                  የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም